# ትንቢት

## ለማስተማሪያ
## እና
## ለጥናት የተዘጋጀ

በዳዊት ፋሲል ተዘጋጀ

2005 ዓ.ም

# 1. <u>በአዲስ ኪዳን ትንቢትን አስመልክቶ ያሉ የተለያዩ አመለካከቶች</u>

## 1.1. ካሪዝማቲክ እና ፔንቴኮስታል ክርስቲያኖች

በአዲስ ኪዳን ያለውን ትንቢት፤"በቀጥታ ከመጽሐፍ ቅዱስ እኩል ስልጣን ያለው ቀጥተኛ የእግዚአብሔር ቃል ነው" ብለው ያምናሉ፡፡ ይህን አስመልክቶ ታዋቂው ፀሐፊ Wayne Grudem "a very word from the lord" ይህም ማለት ከጌታ ቀጥታ እንደተናገረው አድርጎ/በቀጥታ ሙሉ በሙሉ ራሱ እግዚአብሔር እንደተናገረው አድርገው ይወስዳሉ ይለዋል፡፡ የእነዚህኞቹ ክርስቲያኖች ትንቢትን አስመልክቶ የሚንጸባረቀው ዋነኛ የአመለካከት ችግር ትንቢቱ ከመጽሐፍ ቅዱስ እኩል ስልጣን እንዳለው መታየቱ /መወሰዱ ነው፡፡

## 1.2. የተሃድሶ ክርስቲያኖች 16-20ኛው ክ/ዘመን/Traditional/Reformed Church

እነዚህኞቹ አማኞች ደግሞ ቀድሞ በካሪዝማቲክ እና በፔንቴኮስታል ክርስቲያኖች ዘንድ ያለው የአዲስ ኪዳን የትንቢት አገልግሎት ትርጓሜ አግባብ ያልሆነ እና ከመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን እኩል ወይም አንዳንድ ጊዜም ከመጽሐፍ ቅዱስ በላይ ማየታቸው የመጽሐፍ ቅዱስን የሥልጣን ቃል ዝቅ የሚያደርግ ስለሆነ በሚል ፍራቻ ለአዲስ ኪዳን የትንቢት አገልግሎት ሌላ ትርጓሜ አዘጋጅተዋል፡፡ ይህም "የአዲስ ኪዳን የትንቢት ስጦታ በሐዋርያት ዘመን ተነገረ እናም እስከ ተወሰነ ጊዜ ተነገረ ከዛም ግን ተቋርጧል" ብለው ያምናሉ፡፡ እነዚህም ሰዎች "secessionist" ተብለው ይጠራሉ፡፡ የእነዚህኞቹ ቡድን ፍርሃታቸው ምናልባት ሰዎች ልክ እንደ ካሪዝማቲክ እና ፔንቴኮስታል ክርስቲያኖች የአዲስ ኪዳን የትንቢት አገልግሎት ከመጽሐፍ ቅዱስ እኩል አድርገው ከወሰዱት ሰዎች ለመጽሐፍ ቅዱስ ያላቸው ተገዢነት ይወርዳል ብለው ስለሚያምኑ ነው፡፡ ትንቢት ቀርቷል የሚለውን ሃሳብ የወሰዱት ከ1ኛ ቆሮ 13፡8 ላይ ካለው ጥቅስ ነው፡፡ "….ትንቢት መናገር ቢሆን ግን ይሻራል" የሚለውን ንባብ በእንግሊዘኛው "cease" ያደርጋል ከሚለው በመነሳት ትንቢት ተቋርጧል ወደሚለው ድምዳሜ ላይ ይደርሳሉ፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ ለተነሳው ሃሳብ ካሪዝማቲክ እና ፔንቴኮስታል ክርስቲያኖች ምላሽ ሲሰጡ አዎ ትንቢት ይሻራል ነገር ግን የሚሻረው ጊዜው አሁን ሳይሆን "ፍጹም የሆነ ሲመጣ ነው" በማለት 1ቆሮ 13፡10 ላይ ያለውን ጥቅስ ያቀርባሉ፡፡ ይህም ማለት ፍጹም ማለት ሙሉ የሆነ ሲመጣ ማለት ነው ቁ.11 እየበሰለ/እያደገ ሲመጣ ቁ12. በዚያን ጊዜ

ሙሉ እውቀትን ስናገኝ ከፍለን/ግማሽ ብቻ እናውቅ የነበረው ዕውቀት /ትንቢት ነው የሚቆመው ስለዚህ አሁን "በዚያን ጊዜ" የሚለው ስላልደረሰ አሁን ትንቢት cease አድርጓል አይባልምይላሉ፡፡በተጨማሪም 1ቆሮ 1፡7(.....አንድ የጸጋ ስጦታ እንኳ አይጎድልባችሁም፤) ስለሚል ጌታ ሳይመጣ ይህ ትንቢት ሊቋረጥ አይችልም ይላሉ፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ ታዋቂው ጸሐፊ ዋይኒ ግሩደም ሁለቱንም ቡድኖች ይመክራል፡፡ ለካሪዝማቲኮቹ የጸጋ ስጦታን ማበረታታችሁ ልክ ቢሆንም ትንቢትን ግን ልክ ከእግዚአብሔር ቃል እኩል አድርጋችሁ መውሰዳችሁ አግባብ አይደለም ይላቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ሪፎርምድ ቸርቾችን ደግሞ በአዲስ ኪዳን ትንቢት ካሪዝማቲኮች እንደሚሉት ከእግዚአብሔር ቃል ጋር እኩል አይደለም ይልቁንም መንፈስ ቅዱስ በአንድ ሰው አዕምሮ ውስጥ የሚያመጣው ሪፖርት ነው፡፡

በመጨረሻም ትንቢትን አስመልክቶ በዋናነት ስላሉት አመለካከቶች ከላይ የቀረቡ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በዚህ በመጨረሻ ዘመን ላለ አማኝ የተሰጠ ማሳሰቢያ አለ፡፡ ማንኛውም የጸጋ ስጦታ እንደ እግዚአብሔር ቃል ካልተተረጎመ በቀር ልክ እንዳይደለ ወይም ሁሉም ነገር በእግዚአብሔር ቃል መሰረት የሚመዘን መሆኑን ማስተዋል አለባቸው፡፡

<u>**ማስታወሻ**</u>፡-የብሉይ ኪዳን **ነቢያት** እና የአዲስ ኪዳን **ሐዋርያት** ብቻ ናቸው በቀጥታ ስልጣን ያለውን የእግዚአብሔርን ቃል ማምጣት የሚችሉት፡፡ የብሉይ ኪዳን የሥልጣን ቃል የተገለጹት በብሉይ ኪዳን ነቢያት ሲሆን የአዲስ ኪዳን የሥልጣን ቃል የተጻፈው በሐዋርያት ነው፡፡

2. <u>የብሉይ ኪዳን ነቢያት</u>

- የእግዚአብሔርን ቀጥተኛ ቃል የጻፉ ናቸው፡፡
- **ቀጥተኛ የእግዚአብሔር ልዑክ ናቸው**፡፡/በቀጥታ ከእግዚአብሔር ተቀብለው ለሕዝቡ የሚናገሩ ናቸው፡፡ ሐጌ 1፡13፣ አብዲዩ 1፡1፣2ኛነገ 20፡4
- **ቃላቸው ፍጹም የሆነ** /100%/ **የእግዚአብሔር ቃል ነው**፡፡ ነቢያት የሚናገሩት/የጻፉልን ቃል ሙሉ በሙሉ የራሱ የእግዚአብሔር ቃል ነው/ራሳቸው በመንፈስ አድምጠው የተረጎሙት የአዲስ ኪዳን አይነት አሰራር ሳይሆን እግዚአብሔር ራሱ በእነሱ አፍ በቀጥታ የሚናገረው ነው፡፡ዘፀ 4፡12፣ ዘሑ 22፡38፣ ሐዋ 4፡25፣ ዘዳ 18፡18፣ ኤር 1፡9፣ ሕዝ 2፡7፣ ሕዝ 3፡17፣ 2ሳሙ 7፡4፣ 1ኛነገ 13፡26፣
- **ፍጹማዊ መለኮታዊ የስልጣን ቃል ነበራቸው**፡፡ የተናገሩትን አለማመን እና አለማክበር ቀጥታ እግዚአብሔርን ራሱን አለማመን እና አለማክበር ነው፡፡ ዘዳ 18፡19፣ 1ሳሙ 8፡7፣ 1ኛነገ 20፡16

3. <u>የአዲስ ኪዳን ሐዋርያት</u>

የብሉይ ኪዳን ነቢያትን አሁን በአዲስ ኪዳን የተኩት የአዲስ ኪዳን ነቢያት ሳይሆኑ ሐዋርያት መሆናቸውን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል፡፡ ይህም ከላይ ስለ ብሉይ ኪዳን ነቢያት የተጠቀሰውን ባህሪያቶች ሙሉ በሙሉ ሊያሟሉ የሚችሉት የአዲስ ኪዳን /አሁን ያሉ/ ነቢያቶች ሳይሆኑ ሐዋርያቶች ብቻ ናቸው፡፡ ስለዚህ የሐዋርያት ቃል ብቻ ልክ እንደ ብሉይ ኪዳን ነቢያት ቃል ሳይመረመር እና ውድቅ ሳይደረግ የምንቀበለው ነው፡፡

በአዲስ ኪዳን የብሉይ ኪዳን ነቢያትን የሚተኩትየአዲስ ኪዳን ሐዋርያት ለመሆናቸው ሌላው ማስረጃ/ማነጻጸሪያ፡ ዕብ 1፡1-2 (.... ለአባቶች በነቢያት ተናግሮ፣ .... በልጁ ለእኛ ተናገረን)፣ ዕብ 3፡1 (ስለዚህ...የሃይማኖታችንን ሐዋርያ....) ኢየሱስ በዚህ ክፍል ላይ ከብሉይ ኪዳን ነቢያት ጋር ተነጻጽሯል፡፡ ይህም ማለት በብሉይ ኪዳን የነበሩትን ነቢያት የተካው ሐዋርያነት እንጂ ነቢይነት አለመሆኑን ያሳያል፡፡ አሁን በቤተክርስቲያን ያሉት ነቢያት አካሉን ለማነጽና ለመምከር የምንጠቀምባቸው ሲሆኑ የሚናገሩት ቃል ግን ሐዋርያት በጻፉልን መጽሐፍ መሰረት ይመረመራል፡፡በዚህም ላንቀበለው እና ልንጥለው የምንችለው ነገር ይኖራል እንጂ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምዕራፍ እና ቁጥር ተሰጥቶት የሚገባ አይደለም፡፡

እንዲሁም ጴጥሮስ የቀደሙትን ነቢያቶች ያገናኘልን ከአዲስ ኪዳን ሐዋርያቶች ጋር ነው፡፡ በ2ኛጴጥ 3፡2 (በቅዱሳን ነቢያትም ቀድሞ የተባለውን ቃል በሐዋርያቶቻችሁም ያገኛችኋትን...)፡፡በተጨማሪም ሉቃ 11፡49 (...ወደ እነርሱ ነቢያትን እና ሐዋርያትን..)፡፡

- **ሐዋርያት ልክ እንደ ብሉይ ኪዳን ነቢያት ቀጥተኛ የእግዚአብሔር ልዑክ ናቸው፡፡** ለምሳሌ ሐዋርያ ከስሙ ትርጉም ስንነሳ "ሐረ" ማለት በግእዝ ሄደ ማለት ሲሆን apostle /የተላከ፣ መልዕክት ይዞ የሚሄድ ማለት ነው፡፡ስለዚህ ሐዋርያ ማለት የእግዚአብሔርን አዲስ መልዕክት ይዞ ወደ ሕዝብ የሚሄድ ማለት ነው፡፡ዮሐ 20፡21፣ ማቴ 28፡19፣ ሐዋ 22፡21፣ ሐዋ 26፡17
- **የሐዋርያት ቃል ፍጹም የሆነ የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡** ቃላቸው የማንጨምርበት የማንቀንስበት እንዲሁ ልንቀበለው የሚገባ ፍጹም የሆነ የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ ገላ 1፡11
- **ፍጹማዊ መለኮታዊ የስልጣን ቃል ነበራቸው፡፡** በአዲስ ኪዳን ያለ ነቢይ የሚናገረውን ቃል እንደ እግዚአብሔር ቃል ልንመረምረው እንችላለን ነገርግን የሐዋርያትን ቃልና ያስተማሩትን አስተምህሮ አለመቀበል ማለት እራሱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያስተምረውን /ራሱ እግዚአብሔር የገለጠውን ወንጌል አለመቀበል ነው (2ጴጥ 3፡2)፡፡ እንዲሁም ሐዋርያትን ለማታለል መሞከር ማለት መንፈስ ቅዱስን /እግዚአብሔርን ማታለል መሆኑን ያሳያል (ሐዋ 5፡1)፡፡

ስለዚህ ከላይ በቀረበው መሰረት የሐዋርያት አስተምህሮ ተገምግሞ የሚወሰድ እና የሚጣል አለመሆኑ ታይቷል፡፡ በአንጻሩ በአዲስ ኪዳን ያለ የትንቢት አገልግሎትን አስመልክቶ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥልጣን የሌለው በመሆኑ የሚመረመር ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ከተስማማ እንቀበለዋለን ካልተስማማ ደግሞ እንጥለዋለን፡፡ መጽሐፍም፡ ሁሉን ፈትኑ መልካሙን ያዙ ይላል 1ዮሐ 4፡1 (ወዳጆች ሆይ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፤ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደ ሆነ መርምሩ፤ ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋልና፡፡)

በመሆኑም በብሉይ ኪዳን የነበሩ ነቢያትን የተኩት የአዲስ ኪዳን ሐዋርያት ከሆኑ ጌታ ኢየሱስ ለምን አዲስ ስም "ሐዋርያ" የሚል ስያሜ መስጠት አስፈለገው? ለምን ነቢያት ተብለው አልቀጠሉም ብለን እንጠይቅ ይሆናል፡፡ ለዚህም ሦስት ምክንያቶች ነበሩ፡-

1. የነቢዩ የኢዩኤል ትንቢት ነው፡፡ ኢዩኤል 2፡28 (… መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶችልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ….) በብሉይ ኪዳን ትንቢትን የሚናገሩ ነቢያቶች ቁጥር ውሱን ነበር፤ ከዚህም በኋላ ብሎ ነቢዩ ትንቢት ሲመለከት በአዲስ ኪዳን ብዙ ልጆች ትንቢት እንደሚናገሩ ያያል፡፡ ስለዚህ ያ ሁሉ ትንቢትን የሚናገር ሰው ቃሌ የእግዚአብሔር ቃል ነው እንዳይልና በዚሁም አጋጣሚ ብዙ ሃሰተኞች ስለሚሰሩ፤ ይልቁንም ፍጹማዊ የሆነ የቃል መገለጥን በተወሰኑ ቡድኖች "ሐዋርያት" ብቻ በሚገለጠው የእግዚአብሔር ቃል መሰረት እየተገመገመ ለአካሉ ማነጽ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ ስለዚህ ትንቢትን የሚናገር ሁሉ ነቢይ በመባሉ ምክንያት እነዚህ ፍጹማዊውን የእግዚአብሔር ቃል የሚገልጡት አስራ ሁለቱ ደግሞ ከሌሎች ነቢያት ጋር በአንድነት ነቢያት መባል ስለሌለባቸው ሌላ ስም ማውጣት ነበረበት እና ሐዋርያት ተባሉ፡፡

2. ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ወቅት በምድር ላይ የነበረው ሁኔታ፡፡ ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ወቅት የግሪክ ፈላስፎች፣ ቅኔ አዋቂዎች ሁሉ ነቢያቶች ተብለው ይጠሩ ነበር፡፡ ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ አስራ ሁለቱን ሐዋርያት ነቢይ ብሎ ቢጠራቸው እና ወደ ግሪክ ሃገር ቢሄዱ ለሰዎቹ ባለ ቅኔ ወይም ፈላስፎች ናቸው የሚመስሏቸው እንጂ የሰማይን አጀንዳና ሃሳብ ይዘው የመጡ አይመስሏቸውም ነበር፡፡ ለምሳሌ በ40-120 ዓ.ም **ዳዮክሪሶስቶ** ለሃገሩ ሰው ያለመሞት ፍልስፍና ያስተማረ በመሆኑ "prophet of Immortality" ተብሎ ይጠራ ነበር፣ በተጨማሪም **ዲዮጋን**፡የማህበረሰቡን እና የመንግስትን ደካማ ጎን የሚነቅፍና ግልጽነትን የሚያበረታታ በመሆኑ "prophet of truth" ተብሎ ይጠራ ነበር፡፡ እነዚህ ሰዎች ጌታ ኢየሱስን አያውቁም ግን ነቢይ ተብለው ይጠሩ ነበር፡፡ እንዲሁም ጳውሎስ ቲቶ 1፡12 ላይ እነሱ በሃገራቸው ነቢይ ብለው ስለሚጠሩት እርሱም የገዛ ነቢያቸው ብሎ ይላል፡፡

3. ሐዋርያ የሚለው ሥሙ በራሱ ሐዋርያቶቹ ከሚሰሩት ሥራ ጋር የሚመጥን ስለሆነ፡፡ እንደ ቀደሙት ነቢያት ለእስራኤል ሕዝብ ብቻ የተላኩ ሳይሆን ለዓለም ህዝብ ሁሉ የተላኩ በመሆናቸው ሐዋርያ የሚል ስያሜ ማውጣት ነበረበት፡፡

## 4. የአዲስ ኪዳን ነቢያትና የትንቢት አገልግሎታቸው

በአዲስ ኪዳን ያለው የትንቢት አገልግሎት በብሉይ ኪዳን ከነበረው የትንቢት አገልግሎት የተለየ ነው፡፡በአዲስ ኪዳን ያለው ትንቢት ልክ እንደ ብሉይ ኪዳኑ ትንቢት ፍጹማዊ የእግዚአብሔር ቃል መገለጥ ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ሕሊና ውስጥ የሚያመጣው ለወቅቱ የሚያስፈልግ አንዳች የሚመክር፣ የሚያጽናና ወይም ነገሮችን የሚጠቁም ሃሳብና መልዕክት ነው፡፡ ይህም ከብሉይ ኪዳኑ ትንቢት በተለየ ሊመረመር የሚገባው ነው፡፡

- ሐዋ 11፡28 (….በመንፈስ አመለከተ) በግሪኩ "አመለከተ" የሚለው ቃል "ሴማይኖ" ማለት ሲሆን ይህም የሆነ ግልጽ ያልሆነ ነገርን፣ ብዥታን ይገለጻል፡፡ እዚህ ጋር ነቢዩ ረሃብ እንደሚሆን አመልክቷል ግን ረሃቡ መቼ ነው፣ ለምን ያህል ጊዜ ይቆያል፣ ምን ያህል ከባድ ሊሆን እንደሚችል ግልጽ የሆነ መረጃ የለውም፡፡ እንደ ብሉይ ኪዳን ነቢያቶች ሁሉን ነገር በዝርዝር መናገር አይችልም፡፡

- ሐዋ 19:6 (….ትንቢትም ተናገሩ)፡፡ እነዚህ ሰዎች የተናገሩት ትንቢትም አልተገለጸም፤ በመጽሐፍ ቅዱስም ምዕራፍ እና ቁጥር ተበጅቶለት የግድ እንድንማረው፣ የግድ እንድንከተለው የተጻፈ አይደለም፡፡ ይሄ በወቅቱ ለእነሱ የሚስፈልጋቸው አንዳች የሚያበረታ የሚያጸና ቃል በእነሱ መጥቷል፡፡ በተረፈ ፍጹማዊ የእግዚአብሔር ቃል በእነሱ ውስጥ መጥቷል ብለን አንፈልገውም፡፡ በአዲስ ኪዳን ልክ በእነዚህ ሰዎች እንደተገለጠው ነው በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚሰራው፡፡

- ሐዋ 21፡4-14 አጋቦስ ትንቢት ሲናገር ጳውሎስ አልታዘዘም ነበር፡፡ ይህም ማለት ጳውሎስ ትንቢቱ ከእግዚአብሔር ዘንድ አይደለም ብሎ ሳይሆን እንደ ብሉይ ኪዳን ትንቢት ካልታዘዘው ፍርድን የማያመጣ በመሆኑ ነው፡፡ አጋቦስ በመንፈስ ቅዱስ ሆኖ ጳውሎስ ላይ መከራ እንደሚመጣ ይናገራል፤ ጳውሎስም መልዕክቱን ሰምቷል ግን አዎ መከራው ቢመጣብኝም ለዚህ መከራ የተዘጋጀው ነኝ ብሎ ሂደእንጂ የግድ አትሂድ የሚለው ትንቢት ከእግዚአብሔር ስለሆነ ካልታዘዝኩኝ ፍርድ አለ ብሎ አልቀረም፡፡ እዚህ ጋር የትንቢቱ ዓይነት ሊሆን ያለውን ነገር የሚያመለክት ቢሆንም መልዕክቱ በመጣለት ሰው ውስጥ ባለ መንፈስ ጭምር የሚመዘን እና ውሳኔ የሚሰጥበት ነው፡፡

## 5. <u>የብሉይ ኪዳን ነቢያትና የትንቢት አገልግሎታቸው</u>

በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር የሚገናኘው በነቢያት በኩል ነበር፡፡ ትንቢትም እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የሚገናኝበት መንገድ ነው፡፡

- ዕብ 1፡1 (…ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ) ማለት ለእስራኤል አባቶች ማለት ነው፡፡
- ሉቃ 11፡50 አቤልና ዘካርያስ ነቢይ መሆናቸውን ይገልጻል
- ይሁዳ 14 (ሔኖክ ትንቢት ተናግሯል ይላል)
- ዘፍ 20፡7 ለመጀመሪያ ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነቢይ የሚለው ቃል ተገልጦ እናገኛለን፡፡

### 5.1. <u>የብሉይ ኪዳን ነቢያት መጠሪያ ስሞች/ስያሜዎች</u>

- **የእግዚአብሔር ሰው** ተብለው ይጠሩ ነበር፡፡ 1ኛ ሳሙ 2፡27፣ 1ኛ ነገ 13፡1-10፣
- **ባለ ራዕይ** ተብለው ይጠሩ ነበር፡፡ 1ኛሳሙ 9፡9
- **የእግዚአብሔር ባርያ** ይባላሉ፡፡ ኤር 25፡4

### 5.2. <u>የብሉይ ኪዳን ነቢያት ዓይነታቸው</u>

- **አንደኛ ደረጃ /የታወቁ ነቢያት፡፡**እግዚአብሔር ነቢይነታቸውን ያጸናላቸው እና በቀጥታ ነቢይ ብሎ የጠራቸው፤ የብሉይ ኪዳን መገለጦችና ጽሑፎች በእነሱ በኩል ይመጡ የነበሩ ናቸው፡፡ <u>ለምሳሌ</u>፡- ሙሴ (ዘፀ 3)፣ኤሊያስ (1ኛነገ 18፡22)፣ ጋድ (1ኛሳሙ 22፡5). ኢሳያስ፣ ኤርሚያስ፣ ሕዝቅኤል…..

  እነዚህ የታወቁ ነቢያቶች ከሌሎች የነቢያት ዘርፎች የሚለዩበት ምክንያት

  1. ቃላቸው ምድር ላይ አትወድቅም ነበር፡፡ ምክንያቱም ቃላቸው በቀጥታ የእግዚአብሔር ቃል ስለነበር፡፡ 1ሳሙ 3፡19 (…ከቃሉም አንዳች በምድር ላይ አይወድቅም ነበር) ማለት ተሸርፎም ተሰብሮም የሚነገር አይደለም እንዲሁም ተሸርፎም ተሰብሮም የሚፈጸም ሳይሆን በሙላት የሚፈጸም ነው፡፡
  2. እግዚአብሔር የሚናገሩትን ቃል በምልክቶችና ድንቆች ያጸና ነበር፡፡ ለምሳሌ፡- ኤልያስ፡ 1ኛነገ 18፡24-39
  3. የሚተነብዩት ትንበያ በሙላት ይፈጸም ነበር፡፡ 1ኛነገ 14፡8

መጽሐፍትንም የሚጽፉት እነዚህ አንደኛ ደረጃ ነቢያት ነበሩ፡፡

- **ሁለተኛ ደረጃ ነቢያት /የነቢያት ጉባዔ ወይም የነቢያት ልጆች ይባላሉ፡፡** እነዚህኞቹ ነቢያት በዋነኛነት በአንደኛ ደረጃ የታወቁ ነቢያት ስር እንደ ተማሪ /እጅ አስታጣቢ ሆነው የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ በኢየሱስ ዘመን ደቀ - መዝሙር እንደሚባለው ዓይነት ይመስላሉ፡፡

  - 1ኛሳሙ 10፡3-5 እዚህ ጋር ዋናው ነቢይ ሳሙኤል ሲሆን ቀጥሎ ማንነታቸው ያልተገለጸ የነቢያት ጉባኤ እንደሚያገኝ ይገልጻል፡፡ እነዚህ ነቢያት የተናገሩት ቃል እንደ አንደኛ ደረጃ ነቢያት ቃል በመጽሐፍ አልተጻፈም፡፡

  - 1ኛነገ 18፡4 አብዲዩ 100 ነቢያትን ወስዶ የሸሸገ ቢሆንም ስማቸው አይታወቅም፡፡

  - 2ኛ ነገ 2፡3/በቤቴል የነበሩ የነቢያት ልጆች/ ሰዎቹ ኤልያስ እንደሚነጠቅ መገለጥ አላቸው፡፡

  - 2ኛ ነገ 2፡5-7 /በኢያሪኮ የነበሩ የነቢያት ልጆች/

  - 2ኛ ነገ 4፡38 /በጌልጌላ የነበሩ የነቢያት ልጆች/

- **ሴት ነቢያት፡፡** - ዘፀ 15፡20 የሙሴ እህት ማርያም

  - መሳፍንት 4፡4ዲቦራ
  - 2ኛ ነገ 22፡14 ሕልዳና
  - ኢሳ 8፡3 የኢሳያስ ሚስት
  - ነህሚያ 6፡14 ኖዓድያን

እነዚህኞቹም ሴት ነቢያት ልክ እንደ ሁለተኛ ደረጃ ነቢያቶች ሁሉ የተናገሩት ቃል እንደ አንደኛ ደረጃ ነቢያት ቃል በመጽሐፍ አልተጻፈም፡፡

### 5.3. <u>የብሉይ ኪዳን ነቢያት ልዩ መገለጫዎች</u>

5.3.1.በእግዚአብሔር ስልጣንና ውክልና ይላክ ነበር፡፡ ዘፀ 7፡1-2 ሙሴ ለአሮን ውክልና በመስጠቱ እንደ እግዚአብሔር ሆኖ ለአሮን የሚናገረውን ነገር ይሰጠው ነበር፡፡ አምላክ ለነቢያት ትንቢትን እንደሚሰጥ ሁሉ ሙሴም ለአሮን የሚናገረውን ይሰጠው ነበር፡፡

5.3.2.በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ትንቢቱን ለመግለጥ ኃይልን ማግኘት ነበረበት፡፡ ዘኁ 11፡25፣ ሕዝ 2፡1

5.3.3.ትንቢታቸው ሸክም ይባል ነበር፡፡ የሚያመጡት ትንቢት ከበድ ያለ እና ጠንከር ያለ እና በአብዛኛው ለሃገር የሚነገር መልዕክት ሲሆን ትንቢት ከመባል ይልቅ ሸክም ይባል ነበር፡፡ ኢሳ 13፡1፣ 15፡1፣ 17፡1፣ 19፡1፣

<u>ማስታወሻ</u>፡-

በብሉይ ኪዳን ከነበሩት ነቢያት ሁሉ ሙሴ እጅግ የተለየ ነቢይ ነበር፡፡ ሌሎቹን ነቢያት በሕልም፣ በራዕይ እና በሌላም መንገድ የሚናገራቸው ሲሆን ከሙሴ ጋር ግን አፍ ለአፍ፤ ድምጽ ለድምጽ ይናገረው ነበር፡፡ ዘኁ 12፡6፣ ዘዳ 18፡15

### 5.4. <u>የብሉይ ኪዳን ነቢያት ትንቢቱን የሚቀበሉበት መንገድ</u>፡-

5.4.1. ተከታታይ ራዕዮችን ያዩ ነበር፡፡ ራዕይ ማለት ተኝተው ሳይሆን ነቅተው ባሉበት በሕልውና ውስጥ ሆነውvision/ምስል ማየት ማለት ነው፡፡ 2ኛሳሙ 7፡17፣ 1ኛሳሙ 1፡1፣ 6፡1-3፣ ሕዝ 11፡24፣ ኢሳ 1፡1

5.4.2.ሕልሞች ያዩ ነበር፡፡ ኢዮ 33፡14

5.4.3.በአፋቸው ላይ ቃል በማስቀመጥ፡፡ ኢሳ 51፡16፣ ኤር 1፡9

5.4.4.በመንገድ እየሄዱ ወይም በተቀመጡበት በሕሊናቸው ውስጥ እግዚአብሔር ቃሉን ያመጣ ነበር፡፡ 1ሳሙ 15፡10፣ ኢሳ 38፡4

5.4.5. ትንቢቱን ለነቢዩ በግልጽ ለማስረዳት እና መልክ ለማስያዝ መንፈስ ቅዱስ በነቢዩ ላይ በተደጋጋሚ በመምጣት፡፡ 1ሳሙ10፡6፣ ነህ 9፡30፣ ዘካ 7፡12

### 5.5. <u>የብሉይ ኪዳን ነቢያት መልዕክቱን የሚያስተላልፉበት መንገድ</u>፡-

5.5.1. በድምጽ በማሰማት፡፡ በጩኸት፣ “ጌታ እግዚአብሔር፣ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል” በሚል ትንቢቱን በሚያጠናክር መልኩ ይናገሩ ነበር፡፡ ይህም ትንቢቱ በቀጥታ ከእግዚአብሔር የመጣ በመሆኑን ሊፈተን እና ሊመረመር እንደማይችል ለመግለጽ ነው፡፡

5.5.2. ትዕይንታዊ፣ ምልክታዊ በሆኑ መንገዶች መልዕክትን ያስተላልፉ ነበር፡፡ 1ኛነገ 11፡30-35፣ 2ኛነገ 13፡14-19፣ ኤር 19፡10-11፣ ሕዝ 12፡3-6

### 5.6. <u>የብሉይ ኪዳን ነቢያት ዋነኛ ስራቸው እና የትንቢቶቻቸው ይዘቶች</u>፡-

- **ዋነኛ ሥራቸው፡-**

5.6.1. ለእስራኤል ሕዝብ የእግዚአብሔርን /የብሉይ ኪዳንን ሕግ ያስተምራሉ፡፡ 2ኛነገ 17፡13፣ ዳን 9፡10

5.6.2. ለእስራኤል ሕዝብ ይጸልይ ነበር፡፡ 1ኛሳሙ 12፡19-23፣

5.6.3. ምሪትን ይሰጣል፡፡ 1ኛሳሙ 15፡1፣ 9፡9፣

5.6.4. ከእግዚአብሔር መዝሙር እየተቀበሉ ለህዝቡ ያቀብሉ ነበር፡፡ ዘዳ 31፡19፣ 1ኛዜና 25፡1

- **<u>የብሉይ ኪዳን ትንቢት ይዘት</u>፡-**

የብሉይ ኪዳን ትንቢት ይዘት በኪዳናቸው ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ይህም ኪዳን በ623ቱ የሕግ ጽህፈት ላይ የተመሰረተ ነበር፡፡ ዘዳ 28፡1

## 6. <u>የአዲስ ኪዳን ትንቢት ዋነኛ ዓላማዎች</u>

እግዚአብሔር ቤተክርስቲያንን በአዲስ ኪዳን የተገናኛት እንደመሆኑ በዚህ ዘመን የሚነገሩ ትንቢቶች ሁሉ የአዲስ ኪዳን ይዘት ያላቸው መሆን አለባቸው፡፡ 2ቆሮ 3፡4

በአዲስ ኪዳን የሚነገር ትንቢት በዋናነት ሦስት ዓላማዎች አሉት፡1ቆሮ 14፡1-3፣ ሐዋ 15፡32፣ 1ጢሞ 1፡18

1. ለማነጽ፣ ለመገንባት /Edification: አማኙ ካለበት ድካም እንዲወጣፀጋ ማካፈል፡፡
2. ለመምከር /Encourage: ዝሎ የመጣ አማኝ ላይ እምነት ጨምሮ መላክ፡፡
3. ለማጽናናት/Comfort: ያዘነውን አማኝ ማጽናናት

**ፍቅር፡-** <u>**የእውነተኛ አገልጋይ እና አገልግሎት ማረጋገጫ**</u>

1ቆሮ 13፡1. ፍቅር የሌለበት አገልግሎት ከንቱ ነው፡፡ ከአገልግሎት አንዱ የሆነው ትንቢት ሲሆን ፍቅር ግን ከሌለው ይህ አገልግሎት ከንቱ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ፍቅር የእውነተኛ አገልግሎት ማረጋገጫ ነው ሲባል ታጋሽ ያደርጋል፣ ያስተዛዝናል፣ አያቀናናም፣ አያስታብይም… ወዘተ

7. <u>**የአዲስ ኪዳን የትንቢት ምንጮች**</u>

7.1. ከእግዚአብሔር በሆነ መገለጥ /Revelation የሚገኝ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ለመንፈስ የሚያመጣው አንዳች መገለጥ /ምሪት ነው፡፡ 1ቆሮ 14፡29-30.

7.2. ቅጽበታዊ ነው፡፡ ነቢዩ እያሰበበት እና እያሰላሰለው ቆይቶ የሚያመጣው ሳይሆን በቅጽበት ሳይታሰብ መንፈስ ቅዱስ የሚያመጣው መገለጥ ነው፡፡

7.3. የትንቢቱ መገለጥ የሚመጣው ለግለሰብ ነው፡፡ አንድ ዓይነት መልዕክት ለሁሉም ህዝብ የሚሰጥ አይደለም፡፡ 1ቆሮ 14፡29-30 (…ለሌላ ግን አንድ ነገር ቢገለጥለት…)

7.4. መገለጡ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው የሚሆነው፡፡ መገለጡ ከእግዚአብሔር አብ (ማቴ 11፡25)፣ከእግዚአብሔር ወልድ (ማቴ 11፡27፣ ገላ1፡12) ወይም ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ (1ቆሮ 2፡10) የሚመነጭ ነው፡፡ በሁኔታዎች /በሰዎች ላይ ተመስርቶ የሚነገር አይደለም፡፡ ገላ 1፡10

7.5. መገለጡ የሚመጣውና የሚነገረው ከእግዚአብሔር እይታና ፍላጎት አንጻር ነው፡፡

- ትንቢት ማለት እድል መንገር /ጥንቆላ/Fortune Tellers ማለት አይደለም::
- የሰዎችን ፍላጎት ለማርካት የተሰወረ ሚስጢር በመፈለግ የሚነገር አይደለም፡፡
- ነቢዩ በሚናገርበት ወቅት በጣም ጉባዔን በሚያውክ መልኩ የግድ መናገር ላያስፈልግ ይችላል፡፡ 1ቆሮ 13፡8-13፣ 14፡30፡፡ ነቢዩ እራሱን መቆጣጠር አቅቶት

ሞገደኛና ረባሽ በሆነ መልኩ መናገር የግድ አስፈላጊ አይደለም፡፡ በተጨማሪም በሚናገርበት ወቅት አከባቢውን፣ አድማጩን መረዳት ያስፈልጋል፡፡

7.6. ነቢዩ እንደ ብሉይ ኪዳን በቀጥታ ከእግዚአብሔር አፍ የሚቀበል አይደለም፤ ማለት በቀጥታ ሂድና እንዲህና እንዲያ በላቸው የሚል መልዕክት አይሰጠውም፡፡ በተዘዋዋሪ መልክ ከመንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው መገለጥ ነው፡፡

## 8. <u>ሐሰተኛ ነቢያቶች መገለጫቸው</u>

8.1. ለገዛ ጥቅማቸው ወይም ክብራቸው ሲሉ ይተነብያሉ፡፡ ሚኪ 3፡5፣ ቁ.11

8.2. ሰው መስማት የሚፈልገውን ነው የሚናገሩት፡፡1ኛ ነገ 22፡1-37

8.3. ከእግዚአብሔር የሆነውን ሳይሆን ከልባቸው አውጥተው ይናገራሉ፡፡ሳይላኩ ይሄዳሉ፣ እግዚአብሔር ሳይነግራቸው ይናገራሉ፡፡ 1ኛ ነገ13፣ ኤር 23፡9-28፣ ሕዝ 13፡1-16፣ ዘዳ 18፡20-22

8.4. በጌታ በኢየሱስ ስም የተነገሩ ግን ያልተፈጸሙ ትንቢቶችን በሙሉ እግዚአብሔር ፈጽሞ አልተናገራቸውም፡፡ ዘዳ 18፡22

8.5. በኩነኔ መልክ የተነገሩ /አማኙ በክርስቶስ ያገኘውን ሰላም በሚያውክ መልኩ የሚነገሩ ትንቢቶች ሁሉ ፈጽሞ እግዚአብሔር አልተናገራቸውም፡፡

## 9. ትንቢቶችን መመርመሪያ /መመዘኛ /መለኪያ መንገዶች

1ቆሮ 14፡29-30፡፡ በጉባኤ ውስጥ የግድ አንድ ሰው ብቻ ነቢይ ሊሆን አይችልም፡፡ አንዱ እየተናገረ እያለ ለሌላውም አንዳች አዲስ ነገር ከእግዚአብሔር ሊገለጥለት ይችላል፡፡ ስለዚህ በጉባኤ ውስጥ ሁለትም ሦስትም ነቢያት ሊኖሩ ይችላሉ ግን እነዚሁም በየተራ መናገር እንዳለባቸው ተገልጧል፡፡ ከሚናገሩት ውጭ ያሉት ሌሎች ሰዎች ደግሞ ትንቢቱ ትክክል ይሁን አይሁን በጥንቃቄ እንዲመዝኑት፣ እንዲመረምሩት ታዞዋል (1ዮሐ 4፡1)፡፡ ስለዚህ ትንቢት መመርመር /መመዘን ስላለበት መለኪያዎቹ ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፡፡

9.1. በፍሬያቸው፡- የነቢዩ የአገልግሎት ፍሬ፣ የሕይወት ፍሬ፡፡ማቴ 7፡15-20፣ 2ኛቆሮ 11፡13-15፣ 2ኛጴጥ 2፡1-3

9.2. የተነገረው ትንቢት ክርስቶስን ያከብራል ወይ? ትንቢቱን የሚገልጠው መንፈስ ቅዱስ እንደመሆኑ መንፈስ ደግሞ ዓላማው ኢየሱስን ማክበር ስለሆነ የመጣው ትንቢት ኢየሱስን ማክበር ወይም አማኙን ወደ ክርስቶስ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ዮሐ 16፡14፣ ራዕ19፡10፣ 1ኛቆሮ 14፡24-25

9.3. የተናገሩት ነገር ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ይስማማል ወይ?2ጴጥ1፡16-19. መጽሐፍ ቅዱስ የትኛውም ነቢይ ከሚናገረው ትንቢት በላይ "የፀና የትንቢት ቃል" በመሆኑ፡፡

9.4. ተፈጻሚነት /ትንቢቱ ተፈጽሟል ወይ? ዘዳ 18፡20-22

9.5. ትንቢቶች ሁሉ ከእግዚአብሔር እንዳልሆኑ ማወቅ፡፡ ዘዳ 13፡1-5

9.6. ትንቢቱ ለተነገረለት ሰው ነጻነት ነው ወይስ እስራት ነው ያመጣለት? እስራት ማለት ትንቢቱ ከመጣለት በኋላ ያንን ተስፋ በማድረግ ብቻ "ጌታ ተናግሮኛል" ብሎ ስሜቱን፣ ፈቃዱን፣ እውቀቱን ሳይጠቀም መቀመጥ ማለት ነው፡፡ 2ቆሮ 4፡13-15 (የተትረፈረፈውን ፀጋ በአግባቡ መጠቀም አለበት)፡፡

9.7. በቅዱሱ ቅባት መለየት፡፡ 1ዮሐ 2፡20

**"ተፈፀመ"**

☞ ***ዳዊት ፋሲል***

ስ.ቁ0917804407

*ፖ.ሣ.ቁ67ጅማ*

E-mail – besodiyah@gmail.com ወይም niguye2004@yahoo.com